# የመጣባችሁን ከመጣላችሁ ለዩ

ኢብሳ ነመራ 03/11/14

ከቀናት በፊት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን የትምህርት ክፍል ከኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር አንድ የውይይት መድረክ አዘጋጅቶ ነበር። በዚህ የውይይት መድረክ ላይ በተለይ በአሳታፊ ዴሞክራሲና በጥላቻ ንግግር (hate speech) ዙሪያ ጥናታዊ ፅሁፎች ቀረበው ሰፊ ውይይት ተካሂዷል። በውይይት መድረኩ ላይ የሚዲያ ባለሙያዎች፣ ጋዜጠኞች በማህበራዊ ሚዲያ ላይ የጎላ ተሳትፎ ያላቸውን ወጣቶች ጨምሮ ጋዜጠኞች፣ የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች ተሳትፈዋል። በውይይቱ ላይ በመንግስት በኩል የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ፅህፈት ቤት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሽመልስ ከማልና ሌሎችም ተሳትፈው ነበር፡፡

ከተቃወሚ ፓርቲ አመራሮች የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ሊቀመንበር ኢ/ር ግዛቸው ሽፈራው፣ የዚሁ ፓርቲ የቀድሞው ሊቀመንበርና በቅርቡ ከፓርቲው የተሰናበቱት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ እና ዶ/ር ያእቆብ ኃ/ማርያም ተገኝተው ነበር፡፡

የውይይት መድረኩ ላይ በርካታ ጥናታዊ ፅሁፎች የቀረቡ ቢሆንም በተለይ የጥላቻ ንግግርን በተመለከተ የቀረበው ጥናታዊ ፅሁፍን መነሻ በማድረግ የተደረገው ውይይት ሰፋ ያለ ነበር፡፡ መድረኩ የፖለቲካ አቋምን በማንፀባረክ የአቋም ክርክር ከማድረግ ይልቅ አካዳሚያዊ ውይይት ማድረግን ያለመ ቢሆንም፣ ከዚህ ወጣ ያሉ ክርክር ቢጤ የሃሳብ ልውውጦችን አስተናግዷል፡፡

እናም የጥላቻ ንግግርን በተመለከተ የቀረበውን ፅሁፍ መነሻ በማደረግ በተለይ የአንድነት ሊቀመንበር ኢ/ር ግዛቸው ሽፈራውና ትኩስ ነገር ባገኙበት ሁሉ ተቃውሞን በማጋጋል የሚታወቁት ዶ/ር ያዕቆብ ኃ/ማርያም ጉዳዩን የተቃውሞ መግለጫ ለማድረግ ሞክረዋል፡፡ የውይይት መድረኩን የተቃውሞ አቋም ለማንፀባረቂያነት እንዲያውሉት መነሻ የሆናቸው በቅረቡ የአማራ ክልል ምክትል ርእሰ መስተዳደርና የብሄረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን) ዋና ፀሃፊ አቶ ዓለም ነው መኮንን አደረጉት ያሉት ንግግር ነው፡፡ የአንድነት

ሊቀመንበር ኢ/ር ግዛቸውና አጋፋሪያቸው ዶ/ር ያዕቆብ አቶ ዓለምነው ያደረጉት "የጥላቻ ንግግር ነበር" ብለው ተከራክረዋል፡፡

የአንድነት አመራሮች አካዳሚያዊ ውይይት ለማድረግ የተዘጋጀውን መድረክ የተቃውሞ አቋም ለማንጸባረቅ ሊጠቀሙበት የሞከሩት በአጋጣሚ አይደለም፣ ምክንያት አላቸው፡፡ ቀዳሚው ምክንያት ከኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ የመጡት ፈረንጆች መንግስት ላይ ጥርጣሬ እንዲያድርባቸው ማድረግ ነው። አገራቸው ሄደው "የኢትዮጵያ መንግስት አፋኝ፣ ፈላጭ፣ ቆራጭ ምንትስ ቅብጥርስ . . ." የሚል የድርሰት ሪፖርት እንዲቸከችከላቸው፡፡ ይህ ካልሆነም ቀን እየቆጠሩ የኢትዮጵያን ገፅታ የሚያቆሽሽ የፈጠራ ሪፖርት ለሚቸከችኩት "የሰብአዊ መብት ተሟጋች ነን" ለሚሉ ቡድኖች አሳብቀው በዋቤነት እንዲጠቀሱ ለማድረግ ነው፡፡

የአገራችን ፅንፈኛ ተቃዋሚዎች በተለይ ነጮች የኢትዮጵያን ፖለቲካ እንደፈለጉ የማሾር አቅም ያላቸው ስለሚመስላቸው ፈረንጅ ሲያዩ "ተፈለጥን ተቆረጥን" የሚል የፈጠራ ወሬ ማውራታቸው የተለመደ ባሕሪያቸው መሆኑን አስታውሱ፡፡ "አምነስቲ ኢንተርናሽናል፣ ሂዩማን ራይትስ ዎች ወዘተ " የተሰኙት የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ነን የሚሉ የቀለም አብዮት አጋፋሪ ቡድኖች " ኢትዮጵያ ውስጥ የሰብአዊ መብት ጥሰት ተፈፀመ" በሚል የሚያወጡዋቸወ ሪፖርቶች በተመሳሳይ ፈረንጅ ሁሉ በአንድ ቀን ጀምበር የኢትዮጵያን መንግስት አስወግዶ ሥልጣን የሚሰጣቸው የሚመስላቸው ፅንፈኛ ተቃዋሚዎች የሚያወሩላቸው ፈጠራዎች ግልባጭ ነው፡፡

ለፈረንጆቹ ተበዳይ መስሎ ከመታየት በተጨማሪ "የጥላቻ ንግግር ተደረገ" በሚል በባህዳር ከተማ የጠሩትን የተቃውሞ ሰልፍ ተገቢነት ሊያረጋግጡም ነው የውይይት መድረኩን የአቋም መግለጫ ማቅረቢያ ለማድረግ የሞከሩት፡፡ በተለይ ዶ/ር ያዕቆብ ኃ/ማርያም ንግግሩን ከሃያ አመት በፊት የሩዋንዳውን ዘግናኝ እልቂት ካስከተለው በኢንተርሃሞይ ሬድዮ ጣቢያ፣ የቱፕሲ ተወላጆች ላይ ጭፍጨፋ እንዲፈፀም "ኮክሮች ((በረሮዎች) ናቸው" በሚል ጥላቻና ንቀት ከገለፁበት ሁኔታ ጋር ይነፃፀራል ሲሉ ተደምጠዋል፡፡ እርግጥ በውይይቱ ላይ የተሳተፉ ሌሎች ወገኖች ለጉዳዩ በመርህ ላይ የተመሰረተ በቂ ማብራሪያ በመስጠት የተቃዋሚዎቹ አቋም ባዶ መሆኑን አሳይተዋል፡፡

ያም ሆነ ይህ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጋዜጠኝነትና የኮሚኒኬሽን የትምህርት ክፍል ከኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር ያዘጋጀው የውይይት መድረክ ዓላማ በጥላቻ ንግግር ምንነት ላይና በኢትዮጵያ ያለው ገፀታ ላይ አካዳሚያዊ ውይይት ማድረግ ሆኖ ሳለ፣ በተለይ አንድነት ፓርቲ ከዓጀንዳው ማዕቀፍ ወጣ ብሎ አቶ ዓለምነው መኮንን አደረጉት የተባለውን ንግግር “የጥላቻ ንግግር ነው” ብሎ በውይይት መደረክ ላይ የተገኙትን ፈረንጆች በማደናገር አዘኔታ እንዲቸሩት ይህም የፖለቲካ ትርፍ ይሆነው ዘንድ ጥረት ማደረጉ፣ ጉዳዩን በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ርካሽ የፖለቲካ ትርፍ ፍለጋ ማራገቡ የማይቀር መሆኑን ስለሚያሳይ ጉዳዩን በመጠኑ መቃኘት አስፈላጊ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ አንድነት ፓርቲ ከመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ጋር በመተባበር የአቶ ዓለምነውን ንግግር “የጥላቻ ንግግር (hate speech) ነው” በሚል በባህዳር ከተማ የተቃውሞ ሰልፍ ማካሄን አሰታውሱ።

ጉዳዩን ለመቃኘት  የጥላቻ ንግግር (hete speech) ምንድነው? አቶ ዓለምነው የጥላቻ ንግግር አድርገዋል ወይ? ራሱ የጥላቻ ንግግር ተብሎ በፓርቲዎቹ የተወሰደው ንግግር “የጥላቻ ንግግር” ሊባል ይችላል ወይ? የሚሉትን ጥያቄዎች መመልከት ይሻል። በቅድሚያ የጥላቻ ንግግርን ምንነት እነመልከት።

የጥላቻ ንግግር (hate speech) እስካሁን አንድ ሁሉንም ወጥ ትርጉም ባይኖረውምም በተለያዩ ተቋማትና ምሁራን ተቀራራቢ ይዘት ያለው ትርጉሞች ተሰጥቶታል፡፡ ለዚህ ፅሁፍ ዓላማ በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት ያገኘውንና ኮህን- አማልጎርስ የተሰኙ የሕግ ተመራማሪ የሰጡትን ትርጉም መጥቀስ ወድጃለሁ፡፡

ኮሆን-አማልጎርስ የጥላቻ ንግግርን “ከወገንተኝነት ስሜት የመነጨ አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን  በተጨባጭ በሆነውና ‘ነው’ ተብሎ በሚገመት ማንነቱ ላይ ካለ ጥላቻ፣ ምቀኝነት በመነሳት የሚደረግ ንግግር ነው፡፡ የጥላቻ ንግግር የአንድን ቡድን ወይም ግለሰብ የማንነት መገለጫን በተመለከተ አድሏዊ፣ ተፃራሪ፣ ለጥቃት የሚያጋልጥ፣ የጥላቻ ስሜት ይንፀባረቅበታል፡፡ የማንነት መገለጫዎቹ፤ ዘር፣ ሃይማኖት፣ በሂር፣ የቆዳ ቀለም፣ የትውልድ

አካባቢ ሊሆኑ ይችላሉ። የጥላቻ ንግግር ዓላማ የጥላቻ ኢላማ የሆነውን ቡድን ወይም ግለሰብ መጉዳት፣ ሰብአዊ ክብሩን ማዋረድ፣ ማንቋሸሽ፣ ማጥቃትና ጭካኔ የተሞላበት ድርጊት እንዲፈፀምበት በመቀስቀስ ለጥቃት ማጋለጥ ነው" ሲል ይፈታዋል፡፡

የጥላቻ ንግግር በዓለም ላይ በተለይ በሩዋንዳና በቀድሞዋ ዩጎዝላቪያ አስከፊ ሁኔታዎች እንዲቀሰቀሱ ምክንያት መሆኑ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም በዓለም አቀፍ ደረጃ የህግ ማእቀፍ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። እናም ዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት ሰነድ ላይ የጥላቻ ንግግር ምንንት ተገፅጿል። በዚስ ሰነድ ላይ የጥላቻ ንግግርን " በብሄር፣ በዘር ወይም በአንድ ሃይማኖት ተከታዮች ላይ አድልዎ፣ ጥላቻ ወይም ጥቃትን የሚያነሳሳ ማንኛውም አይነት ቅስቀሳ" ሲል ይፈታዋል።

አንድ ንግግር ከተነገረበት አውድ ውጭ ትርጉም ተሰጥቶት "የጥላቻ ንግግር" ነው ተብሎ ለፖለቲካ ጥቅም የሚውልበት ሁኔታ መኖሩን መነሻ በማደረግ የተባበሩት መንግስታት የዘር ማጥፋት ወንጀል ልዩ አማካሪ የሆኑት አዳማ ዲዬንግ ስለጥላቻ ንግግር ሲነሳ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ያሉዋቸውን ጉዳዮች ዘርዝረዋል። ዲዮንግ ስለጥላቻ ንግግር ሲነሳ "ከተነገረበት አውድ (context)፣ ሊያስከትለው ከሚችለው አደጋ፣ ከአደጋው ስፋትና ግዝፈት አኳያ መታየት ይኖርበታል" ብለዋል።

እንግዲህ የአገራችን ፖለቲካ በቅርቡ ያስተናገደውን ከጥላቻ ንግግር ጋር በተያያዘ አቶ ዓለምነው መኮንን አደረጉት የተባለውን ንግግር ከጥላቻ ንግግር ምንነት አኳያ ሲመዘን ምን እንደሚመስል እንመልከት።

አቶ ዓለምነው አደረጉ የተባለው በኢሳት ቴሌቪዥን ያቀረበው ንግግር ይዘት በአጭሩ *አንዳንድ ለእግራቸው እንኳን ጫማ የለላቸው ደሃ አማራዎች የሚናገሩት የትምክህት ንግግር ግን መርዝ ነው፣ ይህ ይትምክህት ንግግር በመከባበርና በመቻቻል ላይ ተመስርተን የገነባነውን አንድነት ለአደጋ ያጋልጣል .* የሚል የዘት ያለው ነው፡፡ ይሄ ከላይ ከተገለፀው የጥላቻ ንግግር ትርጉም አኳያ ሲመዘን እርግጥ የጥላቻ ንግግር ነው ወይ? ይህን ከመመልከቴ በፊት ንግግሩ ተደርጓል ወይ? የሚለውን እንመልከት።

አንድነትና መኢአድ ንግግሩን በቀጥታ ካዳመጠ ሰው አይደለም ያገኙት፡፡ ወይም የፓርቲው አባላት በቀጥታ አላዳመጡትም፡፡ የወሬው ምንጭ "የኢፌደሪን ሕገመንግስታዊ ስርዓት ሽብርተኝነትን ጨምሮ በማንኛውም መንገድ አፈርሳለሁ" ብሎ ከተነሳው ግንቦት 7 የተባለ ቡድን ልሳን ከሆነው ኢሳት ቴሌቭዥን ነው።

"የጥላቻ ንግግር ተደርጓል" ብለው ለተቃውሞ ሰልፍ እንዲወጣ የተደረገው የባህዳር ከተማ ህዝብም "የጥላቻ ንግግር" ተብዬውን በቀጥታ አልሰማም። "ንግግሩ" በአደባባይ የተደረገ አይደለም። በየትኛውም መገናኛ ብዙሃን ባህርዳር ከተማ ባሉት ጭምር አልተቀረፀም፣ አልተላለፈምም። "የንግግሩ" ብቸኛ ምንጭ የአሸባሪውና የኤርትራ ጉዳይ አስፈፃሚው ግንቦት 7 ልሳን የሆነው ኢሳት ቴሌቭዥን ነው። በነገራችን ላይ ኢሳት የተባለው የቴሌቪዥን ጣቢያ በሸአቢያ መንግስት በሚደረግለት ድጎማ ነው የሚንቀሳቀሰው፡፡ ይህን የግንቦት 7 መሪ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ራሳቸው ባለፈው ዓመት በየስድስት ወሩ ከሸአቢያ የሚመደብላቸው ባጀት ሲደርሳቸው የባጀቱን አጠቃቀም አስመልክተው በሰጡት ማብራሪያ በአንደበታቸው መስክረዋል።

የሸአቢያ ጉዳይ አስፈፃሚው የሆነው አሸባሪው ግንቦት 7 ኢትዮጵውያንን አንዱን በሌላው ላይ አስነስቶ ማጋጨት፣ ሕዝብ በመንግስት ላይ መሰረተ ቢስ ጥላቻ (prejudice) እንዲያድርበትና በዚህ ጭፍን መሰረተ ቢስ ጥላቻ ተነሳስቶ መንግስት ላይ እንዲያምፅ ማድረግ ዋነኛውና ብቸኛው የተቋቋመለት ዓላማ ነው። ስለዚህ የግንቦት 7ቱ ልሳን ኢሣት ኢትዮጵያን አስመልክቶ የሚያቀርበው ማንኛውም ዘገባ ከዕውነትነት ይልቅ ሀሰተኛነቱና ሕዝብን ለአመፅ አነሳሽነቱ የጎላ ነው። አንድነትና መኢአድ በዚህ ቴሌቭዥን ጣቢያ ከተላለፈ ዜና ላይ አገኘን ያሉትን ወሬ ይዘው ነው "የጥላቻ ንግግር ተደረገ" ብለው ለተቃውሞ አደባባይ የወጡት።

አቶ ዓለምነው ይህን አደረጉት የተባለውን ንግግር አስመልክቶ በሠጡት አስተያየት፣ "በተቃዋሚ ኃይሎች ሲገለፅ የሰማሁትን ሃሳብ እኔ አልገለፅኩትም፡፡ እኔ አላልኩም! ደግሞስ እኔ ይህንን እንዴት ልል እችላለሁ!? አንደኛ ነገር ለህዝብ ክብር ያለኝ ሰው ነኝ፣ ህዝቦች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸው እንዲከበሩ፣ የመልማት መብታቸው እንዲከበር፣ በራስ መተማመናቸው እንዲጎለብት፣ ከሌሎች የትግል አጋሮቼ ጋር በመሆን የምታገልና

የአቅሜን አስተዋፅኦ የማደርግ ሰው ነኝ፡፡ እንደ ድርጅትም ድርጅታችን ብአዴን በትልቁ የሚፈራውና የሚያከብረው ህዝብን ነው፡፡ ስለዚህ አልክ የተባልኩት ሃሳብ መሰረተ ቢስ ክስ ነው፡፡ እኔ ማንና የማን ሆኜ ነው የራሴን ብሔር ዝቅ የሚያደርግ ሃሳብ የምናገረው? የተወለድኩበትን፣ የወጣሁበትን ብሔር ዝቅ የሚያደርግ ሃሳብ እንዴት ልሰጥ እችላለሁ? እንዴትስ ሊገመት ይችላል? ይሄ በቆርጦ ቀጥል የኮምፒዩተር ዘዴ የተቀነባበረ ሥራ ነው፤ ተቃዋሚዎች አመራሮችን ከህዝብ ለመነጠል የሚያደርጉት ሙከራ ነው፡፡" ብለዋል፡፡

እንግዲህ አቶ ዓለምነው አደረጉት የተባለው ንግግር ከሙሉ አውዱ ውጭ ተቆርጦና ተቀጥሎ የአማራውን ሕዝብ ለማስቆጣት የተበጀ መሆኑን ልብ በሉ። ይህ ተቆርጦና ተቀጥሎ የሸአቢያ ተላላኪ በሆነው አሸባሪው ግንቦት 7 ተቆርጦና ተቀጥሎ የተበጀ ንግግር የአማራ ሥዝብ የክለሉ ገዥ ፓርቲ ብአዴን ላይ መሰረተ ቢስ ጥላቻ እንዲያድርበት ማድረግን ያለመ ራሱ የጥላቻ ንግግርነት ባህሪ ያለው ነው፡፡ አንድነትና መኢአድ በግነቦት 7 በኩል የሻአቢያን ተልዕኮ የማስፈፀም ድርጊት አከናውነዋል ማለትም ይቻላል፡፡

አንድነትና መኢአድ ይህን በእውነት የሌለ፣ ንግግሩ ለመደረጉ አንዳችም ማስረጃ ሊያቀርቡ በማይችሉበት ሁኔታ ነው፤" የጥላቻ ንግግር ተደርጓል፣ ተናጋሪው በይፋ ይቅርታ ይጠይቁ" ያሉት። አቶ ዓለምነው መኮንን ይቅርታ እንዲጠይቁ ያሉት በእጃቸው ላይ ቅጂው በሌለ፣ አንድም አባላቸው በቀጥታ ባልሰማው፣ የትና መቼ እንኳን እንደተደረገ በማያውቁት "ንግግር" ላይ ተመስርተው ነው። ይቅርታ ይጠይቁ ከማለት አልፈው የባህርዳር ከተማን የዋህ ሕዝብ ቀስቅሰው አደባባይ ያወጡትም በዚህ በሌለ ንግግር ነው።

ብዙዎችን ያስገረመው "ጉዳይን ወደ ፍርድ ቤት እንወስዳለን" የሚለው የአንድነትና የመኢአድ ወሬ ነው። ፍቤት ቤት የትኛውን "የጥላቻ ንግግር"፣ የትና መቼ የተካሄደውን ንግግር ሊያቀርቡ ነው። የኢሳትን ቆርጦ ቀጥል የፈጠራ ወሬ ይዘው ከመሄድ ውጭ የሚያቀርቡት አንዳችም ተጨባጭ ማስረጃ የላቸውም፡፡ ይህ ደግሞ ማስረጃ ሊሆን አይችልም፡፡

ስለ ንግግሩ እውነተኛ ያለመሆን፣ የግንቦት 7 ቆርጦ ቀጥል ፈጠራ ስለመሆኑ ይህን ያህል ብዬ፣ የተባለው ንግግር፤ ግንቦት 7፣ አንድነትና መኢአድ ባቀረቡት መልክ ያልተነገረ

መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ተናግሮ እንኳን ቢሆን የአማራ ሕዝብን ኢላማ ያደረገ የጥላቻ ንግግር ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል ወይ? ወደሚለው ጉዳይ ልመለስ።

በፅሁፉ መግቢያ ላይ የጠቀሰኳቸው የ"ጥላቻ ንግግር" ትርጉሞች፣ በቅደሚያ ንግግሩ በሙሉ አውድ (context) ውስጥ መታየት ያለበት መሆኑን ያመለክታሉ። ከአውድ ውጭ ከመፅሃፍ ቅዱስ ውስጥም ቢሆን አንድ አንቀፅ ቦጭቆ የጥላቻ ንግግር ገፅታ መስጠት የሚቻል መሆኑን ልብ በሉ። ከዚህ በተጨማሪ የጥላቻ ንግግር ለራሱ የጥላቻ ዒላማ ለሆነው ቡድን (ብሄር፣ ሃይማኖት . . .) የሚነገር ሳይሆን፣ ተናጋሪው ወገኔ ነው ለሚለው ከንግግሩ ቡድን የሚነገር መሆን ይኖረበታል፡፡ ይህ የሚሆነው "የጥላቻ ንግግር" ተናጋሪው ወገኔ የሚለው ቡድን በሌላ ቡድን ላይ ጥላቻ እንዲያድርበትና ለጥቃት እንዲነሳ የማድረግ ዓላማ ስላለው ነው፡

አቶ ዓለምነው አደረጉት የተባለው ከአውድ ውጭ ተቀንጭቦ የቀረበ ንግግር ራሳቸውም አባል ለሆኑበት የአማራ ብሄር አባላት የተነገረ ነው፡፡ በመሆኑም ሌሎች በአማራ ላይ እንዲነሱ፣ አማራን እንዲጠሉ ማድረግን ያለመ አይደለም። ይሄው ከአውድ ውጭ የተቀነጨበውም "ንግግር" ቢሆን አማራ ከሌሎች የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ጋር በመዋደድ፣ በመከባበርና በመቻቻል በአንድነት እነዲኖር የሚያነሳሳ ነው፡፡ "አማራው ከሌሎች የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ጋር ተከባብረውና ተቻችለው በእኩልነት ንዳይኖሩ ሊያደርጉ የሚችሉ በሌሎች ብሄሮችና ብሄረሰቦች ላይ የሚሰነዘሩ ፀያፍ የትምክህትና የጥላቻ ንግግሮች መወገዝ ይገባቸዋል" የሚል ቃናም ያለው ነው። በመሆኑም ንግግሩ ተነገሮ እንኳን ቢሆን የጥላቻ ንግግር ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል አይደለም።

ተደረገ የተባለው ንግግሩ ዓላማ አማሮች ላይ ጥላቻ ማሳደር ሳይሆን፣ አማሮች ከሌሎች ብሄሮችና ብሄረሰቦች ጋር በአንድነት መስርተው እንዲኖሩ ጥላቻና ንቀትን ማስወገድ አለባቸው የሚል አንድምታ ያለው መሆኑ ከግንዛቤ ሊገባ ይገባል፡፡ ንግግሩ "የሌላው ብሄር ሕዝብ አነሳ ነው፣ አማራ የበላይ ነው" የሚል እምነት ያላቸው ጥቂት ትምክህተኞችን ብቻ የሚመለከትም ነው። ትምክህት የኢትዮጵያን አንድነት አደጋ ላይ የሚጥል በመሆኑ ፀያፍ መሆኑ የተገለፀበት ንግግር ነው። ትምክህተኝነት በፀያፍነቱ የተወገዘበት ንግግር

ነው። እናም ንግግሩ አማራን ሳይሆን ትምክህተኞችን የሚመለከት ነው። እርግጥ ትምክህተኞች ላይ ያለ ጥላቻ በሚገባ ተገልፆበታል። የጥላቻ ንግግር ተደረገብን የሚሉ ቢኖሩ እንኳን ትምክህተኞች ከመሆን ውጭ ሊሆኑ አይችሉም።

ይሁን እንጂ አንድነትና መኢአድ " ንግግሩን የጥላቻ ንግግር ነው" ብለው አደባባይ ወጥተዋል፡፡ የዚህ አይነት ነገር በፖለቲከኞች ዘንድ የተለመደ መሆኑን የሚናገሩ ተንታኞች አንዳንድ ንግግሮች ሆን ተብለው በአንድ ቡድን ላይ ያነጣጠረ ጥላቻ ያዘሉ በሚመስሉበት ሁኔታ ተቃኝተውና ተተርጉመው እንደሚቀርቡ ያስረዳሉ። በዚህ አኳኋን ንግግሮችን ከአውድ ውጭ ቀንጭቦ ያለወጉ በመጠምዘዝ (manipulation ) የተለየ ትርጉም እንዲሰጡ፣ የተለየ ትርጉሙን የተቀበለ የህብረተሰብ ክፍል "የጥላቻ ንግግሩን" አደረገ የተባለ ግለሰብ ወይም ቡድን ላይ ጥላቻ እንዲያድርበት፣ በዚህ ጥላቻ ለጥቃት እንዲነሳሳ የሚደረግበት ሁኔታ አለ ማለት ነው።

ወደሰሞኑ የአቶ ዓለምነው መኮንን ንግግር ስንመጣ ከላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች የጥላቻ ንግግር ተብሎ ሊፈረጅ የማይችል መሆኑ እነደተጠበቀ፣ በግንቦት 7 የጥላቻ ንግግር ገፅታ እንዲኖረው ተደርጎ የቀረበ ሆኖ እናገኘዋለን። አንድነትና መኢአድ ደግሞ የአማራው ሕዝብ መሰረተ ቢስ ጥላቻ አደሮበት በክልሉ ገዢ ፓርቲና መንግስት ላይ እንዲነሳ ግንቦት 7 ያበጀውን ንግግር ተቀብለው በማስተጋባት ዓላማውን ለማሳካት የሞከሩ ሆነው እናገኛቸዋለን።

ይህ የግንቦት 7፣ የአንድነትና የመኢአድ አካሄድ ለአማራ ሕዝብ ከመቆርቆር የመነጨ የአማራን ሕዝብ መብት ማስከበርን ያለመ አይደለም። ከዚህ ይልቅ የአማራውን ሕዝብ በማታለል ለራሳቸው የፖለቲካ ፋይዳ በመሳርያነት መጠቀምን ያለመ ነው። የአማራን ሕዝብ እያምታቱ ለፈለጉት የራሳቸው ዓላማ የሚጠቀሙበት መሳርያ አድርገው የሚመለከቱት መሆኑንም ያመለክታል፡፡ እናም የአማራ ሕዝብ ለወደፊት ሊጠቀምበት የቋመጠን ብልጣብልጥ በትክክል ሊጠቅመው ከመጣ ለይቶ አቋም መያዝ ይጠበቅበታል፤ የመጣለትን ከመጣበት መለየት አለበት ማለት ነው፡፡